# መርህ-ፖሊሲ

BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ መመሪያዎች-ደንቦች፡-** ACA, BFA-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** የትምህርት ቦርድ
ጀነራል ካውንስል

## መርህ -ፖሊሲ ማዘጋጀት

A. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አማካይነት በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ራእይ እና ግብ መርህ-policy ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአገባቡ የፅንስ ሃሳብ ፍቺ ለመስጠት

በቦርድ አማካይነት ሥራ ላይ የሚውሉ መርሆችን ስለማዘጋጀት እና ስለመተግበር ወጥ የሆነ የአሠራር ሒደት ለመመሥረት

በመርህ-ፖሊሲ ዝግጅት ሒደት የትምህርት ቤት ማህበረሰብን መብቶች እና ኃላፊነቶችን በዝርዝር ለማስቀመጥ

B. **ጉዳይ**

ቦርዱ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንትን ምክረሃሳብ በመመርኮዝ፣ የትምህርት ቤት ሲስተምን ትምህርታዊ መርኖች-ፖሊሲዎች መወሰን እንዳለበት የስቴት ህግ ይደነግጋል። ይህንን ሚና በማሟላት ረገድ፣ ቦርዱ ከሌሎች ተግባሮች በተጨማሪ፣ MCPS የሚተዳደርበት መደበኛ መርኖችን ይመሠርታል-ያዘጋጃል። ስለዚህ፣ የመርኖችን ትንታኔ፣ ማዳበር፣ ትግበራ፣ ቁጥጥር፣ እና ግምገማ እና የማህበረሰብ አስተዋጽኦ ሒደት ጋር የሚስማማ ቁልፍ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን (ሠራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/ሞግዚቶችን፣ እና በ "Board Policy ACA" መሠረት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የተለያዩ ብዙሃን የማህበረሰብ አባላትን የሚወክሉ) መርህን-ፖሊሲ የማዳበር ተሳትፎ የሚያበረታታ አጠቃላይ ሒደት Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency-አድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊና ተገቢ፣ እና ባህላዊ ክህሎት ያለው መኖር አለበት።

C. **አቋም**

1. የ MCPS መርኖች እና ደንቦች መምሪያ-የማጣቀሻ መጽሐፍ

   a) ፖሊሲዎች የሚገለጹት እንደ MCPS መመሪያ እና መሠረታዊ ሥርዓት Policies and Regulations Handbook-የፖሊሲዎች እና ደንቦች መምሪያ መፅሐፍበ MCPS ድረ-ገጽ ላይ የቦርድ ፖሊሲ “Board Policy” ተብሎ የተቀመጠ። እነዚህ መርሆች በቦርድ ውሳኔ የፀደቁት እና የተሻሻሉት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ን ራእይ እና ግቦችን ዓላማ ለመዘርጋት፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን መብቶች እና ኃላፊነቶችን በዝርዝር ለማስቀመጥ፣ እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን እና/ወይም የትምህርት ቤት አመራር ሲስተምን መመሪያ ለማዳበር እና ለመተግበር ነው። ሁሉም ፖሊሲዎች ባለሦስት-መለያ ፊደሎች ያሏቸው ሲሆን በ MCPS

ኦንላይን ክፍል ላይ በፊደል ዝርዝር ማውጫ ተቀምጧል የፖሊሲዎች እና ደንቦች አጭር የመምሪያ-የማጣቀሻ መጽሐፍ-Policies and Regulations Handbook፣

b) ደምብ፣ ሥርዓት በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት የዳበረ-የተዘጋጀ የአሠራር መመሪያ ኦንላይን ላይ ይፋ ተደርጓል የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መርኖች እና ደምቦች አጭር መምሪያ/የማጠቀሻ መፅሐፍ-MCPS Policies and Regulations Handbook፣ የቦርድ መርኖችን፣ እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ ህጎችን ስለማስፈጸም።

2. መርህ-ፖሊሲ ማዘጋጀት

a) ቦርዱ ከሦስት ያለነሱ አባላት ያሉት ለሦስት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ በመለጠቅ-በማሠለሥ/staggered የሚሠራ እና አንድ አባል እና የቦርድ ሰብሳቢ ዲሴምበር በሚደረገዉ አመታዊ የቦርድ ስብሰባ ላይ የሚመረጡበት የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ ይኖረዋል። ቦርዱ ለፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አራተኛ ሆኖ/ና በሙሉ አባልነት የሚያገለግል/የምታገለግል የቦርዱን የተማሪ አባል በተጨማሪ ሊመድብ ይችላል። የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው የፖሊስዎችን ረቂቅ ይገመግማል፣ ሀሳብ-አስተያየት ይሰጣል፣ እናም ሙሉው ቦርድ እንዲያፀድቀው ያቀርባል።

b) የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ እና/ወይም ሌሎች የቦርድ አባላት እና ባለድርሻ አካላት በመተባበር መዳበር ያለባቸውን ወይም ክለሳ መደረግ ያለባቸውን መርኖች-ፖሊሲዎች ነቅሰው ያወጣሉ።

(1) የባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ የማድረግ ሒደቶች በሠራተኞች፣ በተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላትን፣ በፖሊሲ ማዳበር አሠራር ተሳትፎ የማበረታታት እና በ "Board Policy ACA" ጋር የሚጣጣም የሞንትጎመሪ ካውንቲን የተለያዩ ማህበረሰቦችን የመወከል ፍላትን ያዳብራልአድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል።

(2) ተማሪዎችን የሚመለከት ዋና ዋና የቦርድ ፖሊሲ ክለሳ ወይም ቀረጻ በሚደረግ ጊዜ የተማሪ ተወካዮች እንዲሳተፉ ይደረጋል። ይህ አይነት አሠራር ተማሪ ተወካዮች በስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ወይም ፖሊሲን በማዳበር ወይም ክለሳ በሚደረግበት በማንኛውም መድረክ የተማሪዎችን አስተዋጽኦ በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል።

(3) የባለድርሻ አካላትን አስተዋጽኦ በተለያዩ ስልቶች-መንገዶች ማሰባሰብ ይቻላል፣ በዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚያካትተው፦ የሥራ ግብረኃይሎች፣ ህዝባዊ ስብሰባዎች፣ እና መረጃዎችን ለመጠየቅ እና ለማግኘት አመቺ የሆኑ ሌሎች ተገቢ የቴክኖሎጂ ስልቶችን በመጠቀም።

(4) የ MCPS ድረ-ገጽ ለባለድርሻ አካላት መረጃ ለመስጠት እና መረጃዎችን ለመጠየቅና ግብረመልሶችን ለማሰባሰብ ጭምር ሊያገለግል ይችላል።

c) የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዮች፣ እና፣ አስፈላጊ-ተገቢ ከሆነ፣ የሚመለከታቸው የሥራ ግብረኃይል አባላት የፖሊሲ ረቂቅ ለማዘጋጀት ይሰበሰባሉ። የፖሊሲ ረቂቁ በአግባቡ ግምት መስጠት ያለበት –

(1) ስለ ቦርዱ ሥልጣን-አመራር፣ ከተልእኮ፣ ግቦች፣ እና ዓላማዎቹ የሚገናኙ ጉዳዮችን ጭምር፣

(2) ሌሎች የቦርድ ፖሊሲዎችን እና ሌሎች መንግስታዊ ኤጀንሲዎችን፣

(3) የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ህጎችን እና መመሪያዎች-ደንቦችን፣

(4) የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን እና ሌሎች ህጋዊ ገደቦችን-ድንጋጌዎችን ወይም ሁኔታዎችን፣

(5) የወጪ አንደምታዎችን፣

(6) በትምህርት ቤት ሲስተም ሥራ ላይ የሚያስከትለውን ፋይዳ-ውጤት፣

(7) ፖሊሲው በሚመለከታቸው ላይ የሚያስከትለውን አንደምታ፣

(8) የብሔራዊ፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ መዛግብት-ጽሑፎች እና ምርምር፣ እና/ወይም

(9) በሌሎች የትምህርት ቤት ሲስተሞች ሥራ ላይ የዋሉ ተመሣሣይ ፖሊሲዎችን እና/ወይም ምርጥ ተሞክሮዎችን።

d) የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ እና አግባብነት ያለው-ያላት ሠራተኛ አማካይነት የፖሊሲ ንድፈ ሃሳቦቹን ለውይይት፣ እና/ወይም ለማሻሻል፣ እና ለጊዜያዊ እርምጃ ለቦርድ ያቀርባሉ።

e) የፖሊሲ ንድፈ ኃሳቡ በውሳኔ የታጀበ ይሆናል –

(1) በጊዜያዊነት የሚቀርበው ፖሊሲ እንደ የመጨረሻ እርምጃ ድምጽ ከመሰጠቱ በፊት ቢያንስ ለ 21 ቀናት በጠረጴዛ ላይ ሳይተገበር እንደሚቆይ ያመለክታል፣

(2) ለዜጎች፣ ለባለድርሻ አካላት፣ እና ለሰራተኞች ሃሳብ እንዲሰጡበት እድል የሚሰጥ መሆኑን፣

(3) ለህዝባዊ ስብሰባ ውይይት የሚቀርብ መሆኑን (ቦርዱ ከፈለገ)፣ እና

(4) ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ምክረኃሳብ እና አስተያየቶችን የመስጠት እድል የሚሰጥ።

f) የመጨረሻ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ፣ ቦርዱ ከህዝብ የተሰጡ አስተያየቶችን፣ ከሠራተኞች የተሰጡ ግብረመልሶችን፣ እና የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አስተያየቶችን ያገናዝባል-ይገመግማል፣ እና ከቦርድ አባላት የቀረቡ ማሻሻያዎችን ማገናዘብ፣ መመርመር ይኖርበታል። ህዝባዊ አስተያየቶች የህዝብ ሪኮርድ አካል ሆነው እንደሚቀመጡ እና ለመጨረሻ ውሳኔ በማኔጅመንት ኮሚቴ አስተያየት ውስጥ በማካተት ለቦርድ የሚቀርብ መሆኑን ህዝባዊ አስተያየቶችን የሚያቀርቡ ሰዎች ማወቅ እንደሚኖርባቸዉ ይመከራሉ። በአስተያየቶቹ ላይ ስለ ግለሰብ ሠራተኛ ወይም ስለ ተማሪ ተለይቶ በሚታወቅ ሁኔታ መካተት የለበትም።

የመጀመሪያው ህዝባዊ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ጉልህ የሆኑ ለውጦች ተደርገውበት ከሆነ፣ ፖሊሲውን እንደገና ህዝባዊ አስተያየት እንዲሰጥበት ተመልሶ እንደሚላክ ቦርዱ ወይም የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው ለቦርድ አስተያየት መስጠት ይኖርበታል።

g) ቦርዱ መወሰን ያለበት እንደአስፈላጊነቱ ወጥነት ያለው ደረጃውን የጠበቀ የፖሊሲ አቀራረብ ይሆናል–

(1) ስለ ፖሊሲው ዓላማ መግለጫ፣

(2) ስለ ችግሩ የሚገልጽ ወይም ፖሊሲው የሚመልሳቸውን እና ለማቅለል የሚመስሉ ጉዳዮችን የሚያብራራ፣

(3) የፖሊሲውን አቋም መግለጫ ወይም የቦርዱን የውሳኔ አቋም፣ የምክንያቶቹን እና/ወይም እንደአግባቡ ይህንን አቋም ለመውሰድ አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶችን፣

(4) የውጤቶቹን መግለጫ ወይም የሚፈለጉትን-የሚጠበቁትን ውጤቶች፣

(5) ፖሊሲውን ለመተግበር-በሥራ ለመተርጎም በመመሪያነት የሚጠቅሙ ስልቶችን/ስትራቴጂዎችን፣ እና

(6) ስለ አፈጻጸሙ እና ስኬታማነቱን፣ ስለተገኙት ውጤቶች፣ እና ቀጣይ እርምጃዎችን በሚመለከት ሪፖርቶች መቼ ለቦርድ እና ለህብረተሰቡ መቅረብ እንዳለባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች። ሪፖርቶች በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንዳለባቸው በቦርድ አማካይነት የሚገለጽ ሲሆን እንደ ህዝቡ ከፍተኛ ፍላጎት፣ ህጋዊ ግዴታዎች፣ እና ስለ ጉዳዩ ሙከራ/የመፍጠር ሁኔታ ላይ የተሞረኮዘ ይሆናል።

3. ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች

በፖሊሲዉ ላይ በቦርድ የተደረጉ ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች ተከታዩ የታቀዱት ማሻሻያዎች ሲያስፈልጉ የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አስተያየት ያቀርባል-

a) የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ ህግ የሚያከብር፣

b) ፖሊሲዉን ይበልጥ በቅርቡ ከፀደቀው የቦርድ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም ለማድረግ፣ እና/ወይም

c) የዝርዝር ማውጫ መረጃዎችን ወቅታዊ ማድረግ (ለምሳሌ፡- የ MCPS ጽ/ቤት ስሞች)። ስለ ጽ/ቤቶች የመረጃ ምንጭን ማመልከት ማለት የተጠቀሰው ጽ/ቤት በሥራ ላይ የሌለ ከሆነ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ወይም ግንኙነት ያላቸውን ጽ/ቤቶች መግለጽ ማለት ነው።

እንደዚህ አይነት በፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ የቀረቡ ቴክኒካዊ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ቦርዱ በፍጥነት መቀበል ይኖርበታል።

4. የፍቺ-የትርጉም አሰጣጥ ህግ

መጣረስ ሲከሰት ከቦርዱ ፖሊሲ ይልቅ የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ህጎች እና ደንቦች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። በቦርድ ፖሊሲዎች መካከል መጣረስ ሲከሰት፣ አዲሱ ፖሊሲ አሮጌውን በመተካት የሚተገበር ሲሆን ነገር ግን በአጠቃላይ መጣረስን ለማስወገድ ለማንበብ ጥረቶች ይደረጋሉ።

5. መርህን-ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ

ከፀደቀ በኋላ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት –

a) አግባብነት ያለው የአፈጻጸም መመሪያዎችን-ደንቦችን ያዘጋጃል፣

b) ፖሊሲዎችን በሙሉ በመምሪያ/አጭር የማጣቀሻ መጽሐፍ ታትሞ እንደአግባብነቱ ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ መሰራጨት፣ እና

c) በሰክሽን "Section F " ግምገማ እና ሪፖርት ስለማድረግ ላይ እንደተገለጸው፣ ፖሊሲውን እና አፈጻጸሙን በተከታታይ መቆጣጠር እና ለቦርድ ሪፖርት ማድረግ።

6. ፖሊሲን ስለማገድ

በህጉ ላይ መደረግ ያለበት ለውጥ በአስቸኳይ የሚያስፈልግ ከሆነና መላውን ሥርዓት ወይም አካል የሚጎዳ ወይም ማንኛውም ፖሊሲ በተናጠል በጊዜያዊነት መታገድ እንዳለበት የሚያመለክት ከሆነ፣ ቦርዱ –

a) የተሟላ የቦርድ ስብሰባ ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ፖሊሲው እንዲወገድ እርምጃ ይወስዳል፣ እና/ወይም

b) በፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አማካይነት ፖሊሲው ክለሳ ተደርጎ መወሰድ ያለበትን እርምጃ ለቀጣዩ የቦርድ ስብሰባ አስተያየት እንዲቀርብ ይመራል።

## D. ተፈላጊ ውጤት

ከመፅደቃቸው ወይም ማሻሻያ ከመደረጉ አስቀድሞ በደንብ የተጠኑ እና ትንታኔ የተደረገባቸው ፖሊሲዎች በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ አማካይነት ቁጥጥር እየተደረገ በሥራ ላይ መዋላቸውን ተከትሎ ውጤታቸው ለቦርድ ሪፖርት መደረግ አለበት።

## E. የአተገባበር ስልቶች

1. ለቦርድ በትክክል ስለማቅረብ፣ ይህንን ፖሊሲ የመተግበር ሥርዓት ያዘጋጃል-ታዘጋጃለች የአፈጻጸም መመሪያዎች፣ የቁጥጥር ሪፖርቶች፣ እና ሥርአቱን ስለመጠበቅ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የፖሊሲ ዝግጅት ጥናትና ምርምር ማስተባበሪያ ጭምር ሥርአት ያዘጋጃል-ታዘጋጃለች።

2. ቦርድ ያጸደቃቸውን ፖሊሲዎች ተመርኩዘው የሚዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎች በሙሉ በመረጃነት ለቦርድ መላክ አለባቸው።

## F. ግምገማ እና ሪፖርት

1. የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው የክለሳውን ወቅታዊ ይዘት መረጃ ሒደት፣ ክለሳ የተደረገባቸውን፣ የተሻሻሉትን፣ በይፋ የተሻሩ-የተሠረዙትን ፖሊሲዎች ጭምር፣ በየወቅቱ መግለጽ-መረጃ መስጠት አለበት።

2. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደት የፖሊሲ ጉዳዮችን በሚመለከት ቅድሚያ የመስጠት አሠራርን ተከትሎ በየወቅቱ ፖሊሲዎችን ይገመግማል፣ ነገር ግን ቦርዱ በራሱ ሥልጣን ያፀደቀውን የትኛውንም ፖሊሲ እንዲገመገም/እንዲከለስ ማድረግ ይችላል። አዲስ ወይም ቀድሞ ያለ ፖሊሲ እንዲዳብር ቦርዱ በሚያዝበት ወቅት፣ የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው ረቂቁን ለተሟላ የቦርድ ስብሰባ ማቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ መስጠት ይችላል።

a) በግምገማው ሒደት ፖሊሲው ላይ የይዘት ለውጥ እንዲደረግ አስተያየት በሚቀርብበት ጊዜ፣ ከዚህ በላይ የተገለጸውን የፖሊሲ ቀረጻ ሒደት ይከተላል።

b) በግምገማው የሚቀርበው አስተያየት-ጥናት ውጤት የሚያመለክተው እንዲሠረዝ ከሆነ፣ የትምህርት ቦርዱ በቀረበው አስተያየት ላይ እርምጃ ይወስዳል።

c) የፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴው ባደረገው ግምገማ ምንም የጎላ ለውጥ እንደማይኖር ሃሳብ ካቀረበ፣ ፖሊሲው በፖሊሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ አማካይነት የተገመገመ መሆኑ “reviewed by Policy Management Committee” ተገልጾ አቀራረቡ ተስተካክሎ፣ በድጋሚ መታተም፣ እና እንደ መረጃ ለቦርድ መቅረብ ወይም መተላለፍ አለበት።

**ተዛማጅ ምንጮች፦** Annotated Code of Maryland, Education Article, §4-108

**የፖሊሲው ታሪክ፦** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 64-92, January 27, 1992; amended by Resolution No. 115-93, February 9, 1993; amended by Resolution No. 341-94, May 16, 1994; reviewed August 27, 1996; amended by Resolution No. 615-01, November 13, 2001; amended by Resolution No. 388-05, July 27, 2005; amended by Resolution No. 250-19, April 9, 2019.

**የቀድሞው ፖሊሲ ታሪክ ማስታወሻ፦** የፀደቀው በውሳኔ ቁ. 425-84, August 7, 1984; amended by Resolution No.430-85, September 10, 1985; amended by Resolution No. 458-86, August 12, 1986; Rescinded by Resolution No. 64-92, January 27, 1992.